# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



# ልዑሉ እረኛ ሆነ


**ጸሐፊው**: Edward Hughes
**የተተረጎመው**: Abel Eshetu
**ምሣሌ አቅራቢው**: M. Maillot; Lazarus
**ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው)**: E. Frischbutter; Sarah S.



ታሪክ 10 ከ 60 ዎቹ መሃከል

**www.M1914.org**

***Bible for Children***, *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


**አማርኛ** Amharic






ሙሴም አካባቢውን ቃኝቶ ማንም አለመኖሩን አረጋገጠ። ግብፃዊውንም ገደለ። በአሸዋም ውስጥ ቀበረው።



3

በማግስቱም ሁለት እስራኤላዊያን እርስ በርሳቸው ሲጣሉ አየ። ጥፋተኛውንም "ወንድምህን ለምንድነው የምትመታው" አለው። ያም "ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትፈልጋለህን?"



4

አለው። ሙሴም፦ ለካስ ያደረኩት ነገር ታውቆአል ብሎ ፈራ። ፈርዖንም ጉዳዩን ስላወቀ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ሙሴም ከቤት ወጥቶ ሸሸ። ወደ ምድያም አገር ሄዶ ተቀመጠ።



5

እዚያም እንደ ደረሰ በአንድ የውሀ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። የምድያም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት። እነርሱም ወደ ውሀው ጉድጓድ መጥተው የአባታቸውን በጎች ውሀ ለማጠጣት ገንዳውን ሞሉት።



6

እረኞችም መጥተው ሲያባርሯቸው ሙሴም ከተቀመጠበት ተነስቶ ተከላከለላቸው። በጎቻቸውንም አጠጣላቸው።



7



ሴቶቹም ወደቤታቸው ሲመለሱ አባታቸው ራጉኤል (ዮቶር) "ዛሬ ያለወትሮአችሁ እንዴት በጊዜ መጣችሁ?" አላቸው። ምክንያቱን ሲያስረዱት አባታቸውም "ጥሩት ይምጣ" አለ። ሙሴም ከዮቶር ጋር ኖረ።

ዮቶርም ትልቋን ሴት ልጇን ለሙሴ ሚስት አድርጎ ሰጠው።

8


በግብፅ አገር ንጉሱ ፈርዖን
ሞተ። የእስራኤላዊያን ሕዝብ
ግን ባርነታቸው ቀጠለ።
እስራኤላውያን ከባርነታቸው
ግፍ የተነሳ
ወደ እግዚአብሔር
አብዝተው ፀለዩ።
ፀሎታቸውም ተሰማ።
9


እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት
እግዚአብሔር ሙሴን ሊጠቀመው
ፈልጓል። ሙሴ ግን አላወቀም።
ከግብፅ ከወጣ አርባ አመታት
አልፈዋል። አሁን እረኛ ነው።
በግብፅ ያሉትን ወገኖቹን
ግን ይናፍቃል።
10


አንድ ቀን ሙሴ በቁጥቋጦ መሀል
እሳት አየ፤ ቁጥቋጦው በእሳት
ቢያያዝም እንኳ አልተቃጠለም።
11


ቁጥቋጠው ለምን እንዳለተቃጠለ
ይህን አስገራሚ ነገር ቀረብ
ብዬ ልመልከት አለ።
12


ሙሴም በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጠው ውስጥ ሙሴ፥
ሙሴ ብሎ ጠራው። እርሱም፦ አቤት አለ። እግዚአብሔርም፦-
ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት
ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።
13


ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ
ፈርዖን እልክሃለሁ። አለው። ሙሴ ግን ለመሄድ ፈርቶ
ነበር።
14

እግዚአብሔር ለሙሴ ታላቅ ኃይሉን አሳየው። የሙሴ በትር ወደ እባብ ተቀየረች።



15

ሙሴ እጁን ዘርግቶ እባቧን ሲይዛት እንደገና በትር ሆነች። እግዚአብሔርም ሌላ ምልክት ሰጠው።



16

እጁንም ወደ ብብቱ አገባት ባወጣትም እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች። እጁንም ወደ ብብቱ መለሳት፥



17

ከብብቱም ባወጣት ጊዜ ተመልሳ ገላውን መሰለች።



18

ሙሴም እኔ ጥሩ ተናጋሪ አይደለሁም በማለት ወደ ፈርዖን ለመሄድ ፈቃደኛ አልነበረም። የእግዚአብሔርም ቍጣ በሙሴ ላይ ነደደ። እኔ ወንድምህ አሮንን እጠቀምበታለሁ። አንተ የሚናገረውን ቃል ንገረው አለው።



19

ሙሴም ወደ ዮቶር ቤት ተመለሰ። ንብረቱን፣ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ግብፅ አገር ሄደ።



20













ልዑሉ እረኛ ሆነ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸአት ምዕ. 2-5

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16